# ስለ ሰው ነፍስ ሕይወት

የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ሕያው ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቅዱሳን መጻሕፍቶችህን ስንመለከት
አስተዋዮች እንሆን ዘንድ ዓይነ ልቡናችንን ግለጽልን ዐይነ ነፍሳችንን አብራልን አሜን! ይሁን ይ
ደረግልን።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የነፍስን አለመሞት የገነትና የሲዖልን መኖር እንመለከታለን። ነፍስ ትሞታለ
ች ገነትና ሲዖል የሉም የሚሉ መሳቲዎች እንደ አሸን ፈልተዋልና።

ይህን ከደካማ አስተሳሰብ የመነጨ ትምህርታቸውን ስናስተውለው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በሕይ
ወታቸው ላይ እንደነገሠና እናዳሻው እንደሚነዳቸው እንረዳለን። ገናና ክቡር ሆኖ የተፈጠረውን
ሰው ተስፋ ከሌላቸውና ለሰው ከተፈጠሩት ከእንስሳት ጋር አስተካክለው «ሰው ከእንስሳ ምንም
ብልጫ የለውም» ማለታቸው፡ ከክርስትና እምነት ወጥተው በሙት ፍልስፍና መጓዛቸውን ይመሰ
ክርባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስንም በስም እንጂ በንባብና በትርጉም አንደማያውቁት ያረጋግጣሉ።

በእርግጥ ወልድ ፍጡር የሚሉ ተረፈ አርዮስ ስለሆኑ ዕጣ ፈንታቸውና ጽዋ ተርታቸው እንደ አባ
ታቸው እንደ አርዮስ ስለሆነ የክብር ትንሣኤ ሳይሆን የአሣር ትንሣኤ እንደሚጠብቃቸው አውቀ
ውት ፈርሰን በስብሰን እንቀራለን ማለታቸው የማይታበል ሃቅ ነው፣ አራዊት ናቸውና እውነቱን
ተናግረዋል። እኛ ግን ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚመሰክረው «በሥላሴ አርአያ የተፈጠርን የማትሞት
የማትፈርስ ሕያዊት ነፍስ ያለን ሰዎች ነን። ጳውሎስ እንዳለ «እኛ የሕያው የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ነን» 2ኛ ቆሮ. 6፣16።

እነሱ ግን አሁንም ጳውሎስ እንደተናገረው «እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መ
ጠን ስለአላከበሩትና ስለአላመሰገኑት በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ፣ የሚያስተውለውም ልባቸው ጨለመ
ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ» ሮሜ 1፣21። ሰውን እንደ እንስሳ አድርጎ ከማመን የበለጠ ድ
ንቁርና የት ይገኛል? እኛ ግን በወንጌል አናፍርምና ይህን የክህደት ትምህርታቸውን በአማናዊውና
መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ትምህርታቸውን የሙት ትምህርት መሆኑን እንገልጻለን።

## በቅድሚያ ስለሰው ተፈጥሮ፣

ሰው በስድስተኛው ቀን «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» ዘፍጥ. 1፣26 በሚለው
አምላካዊ ቃል መሠረት ከአራቱ ባሕርያትና ከደማዊት ነፍስ በመፈጠሩ በማናቸውም ነገር ከእን
ስሳት ጋር ተመሳሳይነት ሲኖረው ነገር ግን ከእንስሳት የሚበልጥበት እግዚአብሔርን የሚመስልባ
ት እንደ መላእክት ፍጹም የማትሞት፣ የማትፈርስ፣ የማትበሰብሰ የምታስብና የምትናገር፣ ዘወት
ር ሕያው ሆና የምትኖር ነባቢት ነፍስ አለችው ዘፍጥረት 2፣7።

እንግዲህ ሰው እንስሳትን የሚመስልበትና መላእክትን የሚመስልበት ሁለት ጠባያት አሉት። እነ
ዚህም ደማዊት ነፍስ፣ ነባቢት ነፍስ ናቸው። እነዚህ ሁለቱ በፈቃድ የማይገናኙ የሚለያዩ ናቸው
። የማይስማሙ የተለያዩ ስለሆኑ ከአራቱ ባህርያት የተፈጠረ ሥጋን ለመማረክ እርስ በርሳቸው
ይዋጋሉ፣ ሮሜ 7፣22

ደማዊት ነፍስ በምታይልበት ጊዜ ሰው እንስሳትን መስሎ ይኖራል፣ ይህም ማለት ሕግ እንዳልተ
ሠራላቸው እንደ እንስሳት ጊዜ ሳይወስኑ መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት፣ መነሳት፣ በልዩ ልዩ ዓ
ይነት ሥጋን ደስ የሚያሰኛትን ሥራ ብቻ ሲሠሩ መኖር ነው። መዝሙር 49፣ 12– 20

ነባቢት ነፍስ ስታይል ሰው መላእክትን መስሎ ይኖራል። ይህም ማለት በጾም፣ በጸሎት፣ በሰጊድ
በቁመት በልዩ ልዩ የትሩፋት ሥራ ተወስኖ ሰማያዊ ነገርን እያሰቡ መኖር ነው።

## የሰው ሞትና የእንስሳት ሞት አንድ ነውን?

አይደለም እንስሳት ሕያዊት ነፍስ ስለሌላቸው አንድ ጊዜ ከሞቱ ከፈረሱ በኋላ ትንሣኤ የላቸው
ም።ዕድል ፈንታቸው ጽዋ ተርታቸው ወደ አፈርነት ተለውጠው ለዘለዓለም መጥፋት ነው።መክ
ብብ 3፣21 ይመልከቱ።«የሰው ልጆች ነፍስ ግን ወደ ላይ ትወጣለች» ይላል። ከዚህም የምንረዳ
ው የሰው ሞት የሥጋና የነፍስ መለያየት መሆኑን ነው። በዚህ ጊዜ ሰው ከአራቱ ባሕርያትና ከደ

ማዊት ነፍስ በመፈጠሩ ከሌሎች ፍጥረታት የሚሻለው መሻል ስለሌለው የማይንቀሳቀስ ሬሳ ሆኖ ይወድቃል። ንቃህ መዋቲ የሚለው የትንሣኤ አዋጅ እስኪሰማ ድረስ ሥጋው በመቃብር ፈርሶ በ ስብሶ አፈር ትቢያ ሆኖ ይኖራል ነፍሱ ግን በባሕርይዋ መፍረስ መበስበስ የለባትምና በደማዊት ነ ፍስ ኃይል ተሸንፋ እንስሳትን መስላ ኖራ እንደሆነ ከአጋንንት ጋር በመከራ ቦታ(በሲኦል) በስቃይ ትኖራለች። ደማዊት ነፍስን አሸንፋ መላእክትን መስላ ኖራ እንደሆነ በዕረፍት ቦታ ከመላእክት ጋር እየተደሰተች ትኖራለች። ሉቃ 16፣ 22 - 26

እንግዲህ ሰው እንደ እንስሳ በሥጋው የሚሞት እንደ መላእክት በነፍሱ ሕያው ሆኖ የሚኖር ስለ ሆነ፣ መጻሕፍት ሰውን በሥጋ መደብ አቁመው ሲናገሩ «ደመና ተበትኖ እንዲሄድ እንዲሁ ወደ ሙታን ሥፍራ የሚወርድ አይወጣም ወደ ቤት ደግሞ አይመለስም ሥፍራውንም አያውቀውም። እንዲሁም ሰው ከተኛ በኋላ አይቆምም ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ (ምጽአት እስኪሆን) በሥጋው ከእንቅልፉ አይነቃምም አይሰማም፣ ልጆቹ ቢከብሩ ወይም ቢዋረዱ አያውቅም አያስተውልም» እያሉ ይናገራሉ፣ ኢዮብ 7፣9-10፤14፣12-24።

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ሰው በሥጋው በመቃብር ውስጥ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረ ስ እንደ እንስሳት ፈርሶ በስብሶ እንደማይቀርና ጌታ በክብር በሚመጣበት ቀን ግን የሰው ሁሉ ሥጋ ከመቃብር እንደ ሚነሳ የሚገልጽ ነው እንጅ፣ ሰው እንደ እንስሳ በሥጋም በነፍስም ይሞታ ል ማለት አይደለም። ኢሳይያስ ስለሞቱ ሰዎች መነሳት እንዲህ ይላል። «ሙታንም ሕያዋን ይሆ ናሉ ( ነፍስ ከሥጋ ጋር ትዋሃዳለች ማለት ነው) ሬሳዎችም ይነሳሉ፣ በምድር የምትኖር ሆይ ጠ ልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩ» ኢሳይያስ 26፣ 19።

የሰው ሥጋ እንደ እንስሳት ሥጋ ፈርሶና በስብሶ እንደማይቀርም ዳንኤል በምዕ. 12፣2 «በምድር ም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ፣ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት፣ እኩሌቶቹም ወደ ዕፍረት ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና» ብሎ ይመሰክራል። እንግዲህ ከላይ በጠቀስናቸው ማስረጃ ዎች መሠረት የሰውና የእንስሳት እድል ፈንታ አንድ እንዳልሆነ ልብ በሉ። እንግዲያው መክብ ብ 3፣19 እንዴት ነው የምንረዳው? ሰሎሞን በዚህ ቦታ ላይ የሰውን ከንቱነት እንስሳት እንደሚ ሞቱት ሁሉ እሱም በሥጋ ሟች ፈራሽ መሆኑን ሊያስረዳን ፈልጎ ነው።

ደግሞ መጻሕፍት ሰውን በነፍስ መደብ አቁመው ሲናገሩ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ከሞቱ በ ኋላ እኔ የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ ይላል፤ ዘጸ 3፣15 እና የሐዋ. ሥራ 7፣ 32 ። እንዲህ ሲል የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አለመሆኑን ይገልጻል። ሁሉም በእርሱ ዘንድ ሕያዋን ናቸውና «የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለሁም ብሎ ጌታ በወንጌ ል ተርጉሞታል » ሉቃስ 20፣38 እና ማቴ. 22፣32 ።

ቅዱስ ጳውሎስም «እኔ በሕይወተ ሥጋ ብኖርም ክርስቶስን ለማገልገል ነው። ብሞትም ዋጋዬ ይ ቀየኛልና በሕይወትም ቢሆን በሞቴም ቢሆን የክርስቶስ ክብሩ በኔ ላይ አለ። እሳቸውን ከሚያሻን ከኒህ ከሁለቱ በአካለ ሥጋ በዚህ ዓለም ከመኖርና በአካለ ነፍስ ከክርስቶስ ጋር ከመኖር ለሰውነ ቴ የምመርጠው ቸገረኝ። መውደዱንስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቼ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እወዳ ለሁ፤ ይልቁንም በሞት መለየቱ ይሻላል» ብሎ በነፍስ ሕያው መሆኑን አስረድቶናል ፊልጲ.1፣ 2 2 - 23።

## <u>የነፍስን ሕያውነት የሚያስረዱ ተጨማሪ ጥቅሶች፤</u>

- <u>መዝ. 30(31)፣ 5</u> «በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ.......» ይህ ጥቅስ የሚያስረዳን የነፍስን ሕያውነትና ሰው በሞተ ጊዜ ነፍሱ በእግዚአብሔር ወይም በሰይጣን እጅ እንደምትወድቅ ነው። ክፉ ከሠራን የሰይጣን እንሆናለን። ሃይማኖታችንን ጠብቀን ከተገኘን ነፍሳችን በእግዚአብሔር እጅ ታሆናለች ፣ በአብርሃምም ጉያ እንሆናለን።

- <u>መክ. 12፣7</u> «...ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ»በሞታችን ጊዜ ነፍሳችን ሕያ ው ስለሆነች ለፍርድ ወደ እግዚአብሔር እንደምትሄድ ይነግረናል።

<u>- ማቴ. 10፣28</u> «ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፣ ይልቅስ ነ ፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ» አንድ ሰው ሞተ የሚባለው በሥጋ መሆኑ ን ነገር ግን ነፍስን ለመግደል ማንም ሰው እንደማይችል ይነግረናል። ምክንያቱም ሕያዊት አድር ጎ ነው የፈጠራትና። ስለዚህ የነፍስ ሞት በገሃነም መጣል ብቻ ነው።

ሉቃስ 23፣46 «.....አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» ጌታ ከእመቤታችን የነሳው ሥጋን ብቻ ሳይሆን ነፍስንም ስለሆነ ሞት ማለት ደግሞ የሥጋና የነፍስ መለያየት መሆኑን ግልጽ ያደርግልናል።

- ዮሐ. ወን. 10፣18 «ነፍሴን በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም» ማለቱ እኛ ነፍሳችን በፈቃዳችን ሳይሆን የምንሰጠው በግዴታ ነው፤ እሱ ግን በፍላጎቱ ነው።

-የሐ. ሥራ 7፣59 «....ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል...» ቅዱስ እስጢፋኖስ ለጌታ ነፍሱን አሳልፎ መስጠቱ ወዳንተ ልመጣ ነው ተቀበለኝ ማለቱ አይደለምን? ታዲያ ነፍስ ሟች ፈራሽ በስባሽ ከሆነች እንዴት ነፍሱን እንዲቀበለው ተጣራ?

-1ኛ ጴጥ. 3፣19 «በሥጋ ሞተ በመንፈስ (በመለኮት) ግን ሕያው ሆነ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወህኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው» ጌታ ቀደም ብለው የሞቱትን በአካለ ነፍስ በዘጠኝ ሰዐት ወደ ሲዖል ወረዶ በሲዖል ላሉት ነፍሳት ነጻነትን ማወጁን የሚናገር አይደለምን? ታዲያ ሰው የምትሞት ፈራሽ በስባሽ ነፍስ ያለው ከሆነ ጌታ ወደ መቃብር ወርዶ ለፈረሰው ሥጋ ነው ነጻነትን የሰበከው? ወህኒ የተባለውም የነፍሳት መኖሪያ ሲዖል ነው።

- ዮሐ. ራእይ 6፣9 «አምስተኛውንም ማህተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያው በታች አየሁ። ......» በሕይወተ ሥጋ በነበሩበት ጊዜ መስዋዕትነትን ከፍለው በአፀደ ነፍስ በክብር ቦታ በሕያዊት ነፍስ መኖራቸውን መናገሩ መሆኑ አይካድም። ሰው በሥጋ ቢሞትም በነፍስ ግን ሕያው መሆኑን ያስገነዝበናል። ለምን አትፈርድልንም የሚሉትስ ሞተው አፈር ትቢያ የሆኑትነፍሳት መሆናቸው ይሆን! ነፍስ ማች ፍራሽ በስባሽ ከሆነች መናገር አይቻላትም። እንግዲህ ሰው በነፍሱ ሕያው መሆኑን ሲነግረን ነው።

ተቃዋሚዎች ትንቢተ ሕዝቅኤል 18፣4 በመጥቀስ ነፍስ ትሞታለች ያላሉ። ቃሉን ግን አበክረን ብንመለከተው ለእነሱ ለራሳቸው ሐሰታዊ ትምህርት መልስ የሚሆናቸው ነው። «ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች» ይህን ብቻ ብሎ አላቆመም። በመቀጠል «ፍርድንና ቅን ነገርን የምታደርግ የጻድቅ ነፍስ በሕይወት እንደምትኖር ተናግሯል፤ ከቁጥር 5 - 9 ይመልከቱ።

«ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች» ሲል ትፈርሳለች ትበሰብሳለች፣ ሕያዊት አይደለችም ማለት ሳይሆን፣ በሲዖል ወይም በገሃነም ስትሰቃይ መኖርዋን መግለጹን ነው» የነፍስ ሞት ሲዖል ወይም ገሃነም መግባት ነው እንጂ እንደ ሥጋ መቃብር መግባት መፍረስ መበስበስ አይደለም።

ነፍስና ሥጋ የተለያዩ መሆናቸው በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም በብዛት ተጠቅሷል፣ የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

–ኦሪት ዘፍጥረት 35፣ 16 - 19 «....እርስዋም ስትሞት ነፍስዋ በምትወጣበት ጊዜ ስሙን ቤንኦን ብላ ጠራችው። ራሔል በምጥ መሞትዋን ሙሴ ሲገልጽ ነፍስዋ ስትወጣ ብሎ ነፍስ ከሥጋ የተለየች፣ ሞትም የነፍስና የሥጋ መለያየት መሆኑን አስረዳ። እንግዲህ ራሔል ራስዋ ነፍስ የምትባል ከሆነ ነፍስዋ ስትወጣ ብሎ እንዴት ሊናገር ቻለ? ወጥታስ ወዴት ሄደች?

—መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17፣ 19 - 23 «........ኤልያስ ይመገብባት የነበረችው መበለት ልጅዋ በሞተባት ጊዘ ኤልያስን እንዲያስነሣላት ለመነችው፣ እሱም ልጅዋን እንድትሰጠው ጠይቆ በአልጋው ላይ አጋድሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጸለየ «አቤቱ አምላኬ ልጅዋን በመግደልህ ይህችን ትቀልበኝ የነበረችቱን ባልቴት እንዲሁ ደግሞ አስጨነቅሃትን? » ብሎ ጮኸ፣ በብላቴናውም ላይ ሦስት ጊዜ ተዘረጋበት፣ ወደ እግዚአብሔርም «አቤቱ አምላኬ ሆይ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ» ብሎ ጮኸ። እግዚአብሔርም የኤልያስን ቃል ሰማ፣ የብላቴናው ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች።

ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ከየት ይገኛል? ነፍስና ሥጋ የተለያዩ ባይሆኑ ሞትም የሥጋና የነፍስ መለያየት ካልሆነ ኤልያስ የልጁን ነፍስ መልስ ብሎ እግዚአብሔርን እንዴት ሊጠይቅ ቻለ? ነፍሱ ብትሆን ኖሮ የሞተችው፣ የሞተችውን ነፍሱን አንሣት ነበር ሊል የሚገባው የብላቴናውም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች ማለት ተለይታው ወደነበረው ሥጋ መጥታ መዋሐድዋን የሚያረጋግጥ አይደለምን?

–መዝሙር 103(104) ፣29« ፊትህን ስትሰውር ይደነግጣሉ፣ ነፍሳቸውን ታወጣለህ ይሞታሉም። ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ» ሞት ማለት የነፍስ መውጣት ወይም ከሥጋ መለየት መሆኑን ዳዊት ግልጽ አድርጎ አስፍሮታል። ነፍስ በምትወጣ ጊዜ ሥጋ በድን ይሆናል፣ ወደ አፈርነቱም ይ

መስሳል። እስከ ጊዜ ምጽአት ድረስምፈርሶ በስብሶ ይቆያል። በመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጊዜ ሰው ለማለት ነፍስ በማለትም ይጠራል ለዚህም ማስረጃ ብንፈልግ የሐዋ. ሥራ 14፤7 ያዕቆብ ሰባ አምስት ነፍስ ሆኖ ወደ ግብጽ መውረዱን ይናገራል። እዚህ ላይ ሥጋን በነፍስ ስም ሲጠራ ነው እንጂ ሥጋቸው በከነዓን ቀርቶ ነፍሳቸው ተለይታ ግብጽ ወረደች ለማለት አይደለም።

<u>የጻድቃን ነፍስ ጊዜያዊ መኖሪያ ስለሆነችው ስለ ገነት</u>

መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ አንብበው ያልተረዱ ሰዎች ሰው ራሱ ነፍስ ስለሆነ በሞተ ጊዜ ነፍሱ ትሞታለች እና የሰው ሁሉ መኖሪያ ከሞተ በኋላ መቃብር ነው እንጂ ገነትና ሲዖል የሉም ይላሉ። ይህ ግን ፍጹም ሐሰት የሆነ ትምህርት ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው ሕያዊት ነፍስ እንዳለች በተረዳ ነገር አውቀናል። እና የሕያዊት ነፍስ መኖሪያ የት ነው? ነፍስ ሕያው ከሆነች ከሞተች በኋላ መኖሪያ ይኖራታል። ሲያልና ገነት የኃጥአንና የጻድቃን ነፍስ መኖሪያ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገነት መኖር እንዲህ ሲል ያስረዳናል። ዘፍ. 2፤ 8 - 15 የገነት መዘጋጀት ይነግረናል።

– <u>ኢሳይያስ 51፤ 3</u> «ምድረ በዳውን እንደ ኤደን አንደ እግዚአብሔር ገነት....» እዚህ ላይ ገነት የምትባል እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያዘጋጃት መኖርዋን መግለጹ ነው። ይህቺ የምንኖርባት ምድርም አለመሆንዋ ግልጽ ነው።

– <u>ትን. ሕዝ. 36፤35</u> «ባድማ የነበረች ይህቺ ምድር እንደ ኤደን ገነት ሆናለች» ብሎ ይህቺ ዝሙት ምንዝርነት የበዛባት ምድር ሳትሆን ገነት የንጹሃን መኖሪያ ደስ የምታሰኝ ቦታ መሆንዋን ይገልጽልናል።

የገነትን መኖር የሚክዱ ክፍሎች «ገነት ከጥፋት ውኃ በፊት ነበረች ኋላ ግን ምድር በውኃ በጠፋች ጊዜ እርሷም ጠፍታለች» ይላሉ። ይህን ዐይን ያወጣ ውሸታቸውን ከየት እንዳገኙት ባላውቅም በመጽሐፍ ቅዱስውስጥ ግን እንዳልሰፈረ እርግጠኛ ነኝ። እስቲ እነዚህን ወተቱን አጥቁረው፣ ማሩን አምርረው ለተናገሩ መስቲዎች አንድ ጥያቄ ላቅርብላቸው፤ በጥፋት ውኃ ጊዜ ለመሆኑ ይህቺ አሁን ያለንባት ምድርስ ጠፍታ ነበር ወይ? ምድር በንፍር ውኃ ጠፋች ሲባል ምድሪቱ ሳትሆን በውስጥዋ ያሉት ሰዎችና እንስሳት መሆናቸውን ቢረዱ ኖሮ እንዲህ ዓይነት ቅሌት ውስጥ ባልገቡ ነበር። እንደ እነሱ አባባል ቢሆንማ ይህችም ምድር ጠፍታለሁለተኛ ጊዜ ነው የተፈጠረችው ማለት ነው። ምክንያቱም በኖህ ዘመን መላ ዓለም ጠፋች ብለው ያምናሉና። ዓለም ሲባል በምድር ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችዋ መሆናቸውን ማን በነገረልን። እኛ ግን ይህን ከጥርስ ተርፎ ዓይን የሚያስቀውን ቀልዳቸውን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሳችን አፈር ትቢያ እናለብሰዋለን

– ሉቃስ 23፤ 43 «ጌታ ኢየሱስም እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው» ቆርጦ ቀጥሎች ይሄን ቃል ምን ይሉት ይሆን? ገነት በኖህ ዘመን የጠፋች ከሆነ ጌታ በገነት ዛሬ ከእኔ ጋር ትኖራለህ የሚለው? የሌለባትን ከዚህ ከኖረባት ምድር ለየት ያለች ፍጹም የተድላ ደስታ ቦታ ስለሆነች ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ አለው እንጂ። ሲያልንስ በመቃብር መስለዋታል፣ ገነትንስ በምን ይመስሉአት ይሆን።

– 2ኛ ቆሮ. 12፤ 4 «...ወደ ገነት ተነጠቀ ሰውም ሊናገር የማይገባውን ቃል ሰማ» ወደ ገነት ተነጠቀ ማለቱ ከዚህች ካለንበት ዓለም ለየት ወዳለች ቦታ ተወሰደ ማለት አይደለም? ሰውስ ሊናገረው የማይገባ ቃል በዚህች ምድር ላይ ይኖር ይሆን? በገነት ግን ብዙ የሚያስደንቁ ነገሮች አሉና እነኛን ሁሉ ማየቱን ነገረን።

–ራዕይ 2፤7 «ድል ለነሳው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ አሰጠዋለሁ» ገነት ይህች የምኖርባት ምድር ከሆነች በውስጥዋ የሚገኙት ፍራፍሬዎች ያለምንም መስዋዕትነት በገንዘባችን ገዝተን እንበላቸዋለን። መታገልና ድል መንሳት አያስፈልግም። ደግሞም በዚህች በምንኖርባት ምድር ላይ ሕይወትን የምትሰጥ የሕይወት ዛፍ የለችም። እንግዲህ ጻድቃን በዚህች ምድር ላይ ከዲያብሎስ ጋር ተዋግተው ድልሲነሱ በገነት ይኖራሉ።

<u>ስለሲያል ፤</u>

ጻድቃን ሲሞቱ ነፍሳቸው በገነት እንደምታርፍ በአንጻሩ ደግሞ የኃጥአን ነፍስ መኖሪያ ሲያል ነው። እስከ ዕለተ ምጽአት ነፍሳት በሁለቱም ሥፍራ ይኖራሉና። ሲያል ማለት ጉድጓድ ወይም መቃብር ማለት ነው ጉድጓዳውን ቦታ ሁሉ ሲያል ይለዋል በሲያል ይመስለዋልና።

**የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ፣**

–**መዝ.** 15(16)፣ 9 - 10 **«ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና» ይህ አነጋገር የሥጋና የነፍስን መኖሪያ የተለያየ መሆኑን ያመለክተናል። ልበ አምላክ ዳዊት ከክርስቶስ መወለድ ሺ ዓመትቀደም ብሎ የነበረ ሰው ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩ ጽድቅ ሥራ የሠሩም ሆኑ የኃጢአት ሥራ የሁሉም ነፍስ የተስፋው ቀን እስኪፈጸም ወደ ሲኦል ነበር የምትወርደው። ዳዊትም ጌታ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ነጻነትን ሰብኮ ከሲኦል እንደሚያወጣው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ሲናገር «ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች፣ በመጨረሻው ዘመን ነፍሴን ተዋሕዳ ስለምትነሳ» ብሎ ሥጋው ሞቶ ፈርሶና በስብሶ እንደማይቀር ጭምር ተናገረ።**

–**መዝሙር** 9፣ 17 **«ኃጢአተኞች ወደ ሲኦል ይወርዳሉ» ይህን አባባል ተቃዋሚዎች ወደ መቃብር ነው። የሚወርዱ ካሉ ኃጢአተኞች ብቻ ሳይሆኑ ጻድቃንም ጭምር ናቸው። ሙሴ እራሱ በመቃብር ተቀብሯል። ኧረ ሌሎችን ቅዱሳን ትተን የእውነት ንጉሥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እራሱ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሯል። እንግዲህ ሲኦል ማለት መቃብር ማለት ከሆነ ጌታንም ኃጢአተኛ ሊሉት ነው?**

–**ምሳሌ** 15፣ 24 **«በታች ካለው ከሲኦል መንገድ ያመልጥ ዘንድ የሕይወት መንገድ አስተዋዩን ሰው ወደ ላይ ይወስደዋል» የሲኦል መንገድ የተባለው ኃጢአት ሲሆን የሕይወት መንገድ የተባለው የጽድቅ ሥራ መሆኑ ግልጽ ነው። እንግዲህ ሰው ሁሉ በሚሠራው ኃጢአት ወደ ሲኦል፣ በሚሠራው የጽድቅ ሥራ ወደ ገነት እንደሚገባ እንወቅ እናስተውል።**

– **ሉቃስ**16፣ 22 - 31**«እዚህ ላይ የኃጠአተኞች ነፍስ በሲኦል በሥቃይ እንደምትኖር ጌታ ራሱ በማይታበል ቃሉ ገልጾልናል ምሳሌ ነው ቢሉ በሌለ ነገር መስሎ አልተናገረም። በሌለ ነገር እንኳን ጌታ ሰውም አይመስልም። ደግሞ የሌለን ነገር እንደ ውሸታም ሰው ያለ አስመስሎ አወራ ማለት ፍጹም ኃጢአት ነው። እሱ የእውነት አባት መሆኑ በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጿልና።**

– **ራዕይ** 20፣ 13 **የሲኦልን መኖር ይገልጽልናል።**

**ማጠቃለያ**

1/ **ምቹ የአትክልት ቦታ ሁሉ ገነት እየተባለ ይጠራል ይህም በገነት ምሳሌ መጥራት ነው እንጂ ከመንግት ሰማይ በታች ከምድር በላይ መካከል ያለች ገነት የምትባል የጻድቃን ነፍስ መኖሪያ የለችም ማለት አይደለም። አዳምና ሔዋን ሳይሳሳቱ ይኖሩባት የነበረ ገነት ከምድር በላይ ከሰማይ በታች እንደነበረ እናምናለን። ጌታ በክበበ ትስብዕት በግርማ መንግሥት በሚመጣበት በዕለተ ምጽአት «እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ» ብሎ ጻድቃንን የሚጠራቸው ከገነት «ሒዱ ብሎ» ኃጥአንን ወደ ገሃነም የሚያሰናብታቸው ከሲኦል ነው ምክንያቱም ገነትና ሲኦል የነፍሳት ጊዜያዊ መቆያዎች ናቸው።**

2/**ሲኦል የለም ማለት አይደለም ሲኦል የስቃይ ስፍራ ስለሆነ ማናቸውንም የስቃይ ስፍራዎች በተለምዶ ሲኦል እያልን እንጠራቸዋለን። ደስ የሚያሰኘን አትክልት ያለበትን ቦታ ገነት ነው እንደምንል ሁሉ የስቃይንና የመከራ ቦታ የሆነውንም ደግሞ ሲኦል ነው እንላለን።**

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር።**

**ዓምደ ሃይማኖት ከሚለው ብርሃኑ ጎበና በ**1992 **ካሳተሙት የተወሰደ።**